# ለአደጋ ተጋላጭነትን መቀነስ ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውርን መቆጣጠር

የዓለም ሕዝብ ሰላምና ሕልውናው ተረጋግጦና ሀገራት በየራሳቸው ባህልና ወግ መኖር እንዲችሉ መንግሥታት ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ከጀመሩ ዘመናት ተቆጥረዋል። በነዚህ ጊዜያት ሁሉም የዓለም ሕዝብ ሰላም ወዳድ ነው ብሎ ማሰብ ግን አልተቻለም። የሰላምና የዴሞክራሲ መስፈን የእግር እሳት የሆነባቸው አንዳንድ አሻባሪዎች የራሳቸውን ፀረ-ሰላም መረብ በዘረጉ ዓመታትን አስቆጥረዋል።

የእነዚህ አሻባሪዎች አጀንዳ ሽብርን ማስፈን፣ ሀገራት በተለያዩ ምክንያቶች እንዲቃረኑ ማድረግና እልቂትን ማስከተል ነው። ለዚህም መፍትሔ የተባሉ ጉዳዮች ሁሉ ተሚጠው እስኪያልቁ ድረስ የሀገራቱ መንግሥታት ብርቱ የሆነ የደህንነት ፖሊሲና ስትራቴጂ አውጥተው መንቀሳቀስ የግድ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያም ለነዚህ ፀረ-ሕዝብ ኃይሎች አልተንበረከከችም። ይህንንና መሰል ችግሮችን ለመቆጣጠር በስፋት በመንቀሳቀስ ላይ ትገኛለች።

በአገራዊ ጥቅምና ህልውና ዋነኛው አደጋ ድህነታችን፣ ኋላቀርነታችንና የዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር ሥርዓት ስር አለመስደድ እንደሆነ በተደጋጋሚ ተገልጿል። አገራዊ ጥቅማችንም ሕልውናችንን ለማስጠበቅ በዋነኛነት በአገር ውስጥ በሚካሔድ ርብርብ እነዚህን የሥጋት ምንጮች ማድረቅ እንደሚገባንም ግልጽ ነው። ከውጭ የሚመጣ አደጋም በዋናው የሥጋት ምንጭ ላይ የተመሠረተ መሆኑ አይቀርም። ምክንያቱም ከውጭ የሚመጣ አደጋ አንድም ከውስጥ አደጋ ጋር ተሳስሮና ተቀናጅቶ ተፈጻሚ ይሆናል። አሊያም የውስጥ ድክመትንና ለአደጋ ተጋላጭነትን ታሳቢ በማድረግ ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያዎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ሊፈጸም ይችላል። እስከ ዛሬ ድረስ በአገራችን ላይ የተቃጡ የውጭ አደጋዎችን በምንመረምርበት ወቅት የምናረጋግጠውም እውነታ ይህንኑ ነው።

በዚህ ረገድ አገራችን ድሃና ኋላቀር በመሆንዋ የኢኮኖሚና ሌሎች ተፅዕኖዎችን በማሳረፍ ማንበርከክ ይቻላል በሚል ግምት አገሮች ኃይሎች ጥቅማችንና ደህንነታችንን የሚፈታተን ነገር ሊጭኑብን ሊደፋፈሩ ይችላሉ። ሕዝቡ በአንድነት ለጋራ አላማ አይረባረብም፤ እርስ በርሱ በቀላሉ ሊናቆር ይችላል በሚል መሰረት የሌለው መላምት ከሀገራችን ላይ ሥጋትን የሚያሳድር ችግር ለመፍጠር ለመነሳሳት ይሞክራሉ።

ለአደጋ የሚያጋልጡን ውሱንነቶች መኖ ራቸው ብሔራዊ ጥቅማችንና ደህንነታችንን በሁለት መልኩ ይፈታተናል። በመጀመሪያ ደረጃ እነዚህ ጥቅሞችና አደጋዎች እንዳይከሰቱ ከውጭ የሚመነጩ ስጋቶች በእንጭጩ እንዳይቀጩ እንቅፋት ይሆናል። ስለዚህም ለአደጋው ተጋላጭ ባንሆን ኖሮ ሊኖር ይችል ከነበረው በላይ ለግጭትና ለጦርነት የተጋለጥን እንሆናለን። በዚህ መሠረት ለምሣሌ ዚያድ ባሬ ኢትዮጵያ በቀላሉ ልትበታተን ትችላ ለች፣ ለአደጋ የተጋለጠች ነች ብሎ በመገመቱ ሠራዊቱን አሰማራ። ሻዕቢያም ከውጭ ጥቃት ከፈጸምኩ ተባብሮ የሚመክተኝ አቅም አይኖርም፤ ይበታተናል ብሎ በማሰቡ ወረራ ፈፀመብን፡ በርግጥ የሁለቱም ግምት የተሳሳተ ስለነበር ሁለቱም ክፉኛ ተመተዋል። ይሁንና ይህ እስኪሆን ድረስ በጦርነት ጠምደውናል ከፍተኛ ጉዳትም አድርሰውብናል።

የአደጋ ተጋላጪነታችን ዋንኛ ምንጭ ድህነታችንና ኋላቀርነታችን ነው። ለውስጡም ለውጭውም አደጋ በዋነኛነት የሚያጋለጠንም ይኸው ነው። በመሆኑም ከሁሉም ነገር በላይ ይህንኑ በፍጥነት መቅረፍና በደትም ለማስወገድ መሥራት አለብን። ለዚህም ሁሉም ነገር ሊፋጠንና ሕዝቡን በየደረጃው ተጠቃሚ ለሚያደርግ ልማት መዋል አለበት ወደሚል አቅጣጫ መንዝ ይኖርብናል። ይህ ሲሆንም ከዚህ ውጪ የሆኑ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎችN ለዚሁ ዓላማ ተገዥ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈ ልጋል።

የውጭ ጉዳይና የአገራዊ ደህንነት ግቦቻችንን ለማሳካት የምንከተለው አንዱ መሠረታዊ ስትራቴጂ ለአደጋ ተጋላጭነታ ችንን መቀነስ ነው። የዚህን ምንጭ ማግኘት ለዘላቂ የሀገራችን ልማት፣ ዴሞክራሲ መስፈን ዓብይ አስተዋፅኦ ያደርጋል። ይህን ከግቡ ለማድረስ ዋናው መፍትሔያችን ልማትና ዴሞክራሲ በመሆኑ አደጋ ብለን የምንለው ይህንን ዓላማ የሚያሰናክልብንን ነገር ነው። ስለሆነም አደጋ ከየት ሊመጣብን ይችላል የሚለውን ጥያቄ በጥናት መመለስ አለብን። ለዚህም መነሻችን በዋነኛነት የእኛ ልማትና የዴመክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሥራ መሳካትን ጥቅማቸውን ሊቀንስላቸው የሚችሉ ወገኖችን እነማን ናቸው ብሎ ማጥናት አስፈላጊ ይሆናል።

በመሆኑም ይህ ጉዳይ የጥቂት ሙያተኞች ወይም የፖለቲካ ኃላፊዎች ሥራ ተደርጎ መወሰድ የለበትም። የተሳካ አፈፃፀም ሊኖር የሚችለውም መላው ሕዝብ እንደ ሁኔታው ሲሳተፍበት ነው። በተደጋጋሚ እንደ ምንገነዘበው ድህነታችንን ጥገና አድርገው ወደእያንዳንዳችን ቤት እንኳ የሚመጡ ብዙ ሕገወጥ እንቅስቃሴዎች አሉ። ከእነዚህ ውስጥ ዋነኛው ሕገወጥ የመሣሪያ ዝውውር ነው ማለት ይቻላል።

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የዚህ የሕገወጥ እንቅስቃሴ ገፈት ቀማሾች እኛ መሆናችንን መዘንጋት የለብንም። ዛሬ እንደምናውቀው የሕመሙ፣ የስቃዩ የሞቱና የውድመቱ ፅዋ ጠጪዎችም እኛው ራሳችን መሆናችን፣ ድርጊቱን አስገራሚና አሳዛኝ እያደረገው ይገኛል። እህት፣ ወንድም፣ ጓደኛ፣ ዘመድ እና ሀገርን የማጥፋት እንቅስቃሴ ውስጥ ለመሳተፍ ድህነትን መዋጋት ፈፅሞ ውጤት አይኖረውም። ድህነትን መዋጋት የምንችለውም ማንም ቢሆን መገንዘብ አያዳግተውም።

ሕጋዊ የድህነት ቅነሳ መሠረቱ ልማትንና የዴሞክራሲን ሥርዓት የማስፈን እንቅስቃሴ መሆኑን መንግሥት በተለያዩ መንገዶች ለዜጎች እያሳወቀ ይገኛል።

የዚህን ሕገ ወጥ የመሣሪያ ዝውውር ከሀገር ሀገር አስከፊ ደረጃ ላይ መድረሱንና እያስከተለ ያለውም መሪር ሞትና ወድመትን አንድ ሀገር ብቻዋን የማትወጣው ሆኖ በመገኘቱ በ2004 እ.ኤ.አ በቡሩንዲ፣ በዲ.ሪ.ኦፍ ኮንጐ፣ ጅቡቲ፣ ኤርትራ፣ ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ሩዋንዳ፣ ሱዳን፣ ኡጋንዳ፣ ሲሸልስ፣ ሶማሊያ እና ታንዛኒያ መካከል ሕገወጥ የመሣሪያ ዝውውርን ለመከላከልና ለመቀነስ የሚያስችል በአፍሪካ ቀንድ ታላላቅ ሐይቆች ማስተባበሪያ ማዕከል የናይሮቢ ፕሮቶኮልን ተፈራርመዋል።

ኢትዮጵያ ወዲያውኑ መስከረም 29 2004 በሀገር ውስጥ የሚከሰተውን ችግር ለመከላከል የሚያስችል ብሔራዊ የትኩረት አቅጣጫ መሥርታለች። ይህ የሀገራችን ተግባር ከአባል ሀገራት የመጀመሪያዋ ቃልን ያከበረች አድርጓታል።እነኚህ ሀገራት የጦር መሣሪያን ለችግር መፍቻነት መጠቀም የለባቸውም። ምክንያ ቱም ጦር

*መሣሪያ ግጭቶችን ያሰፋፋል። ቅራኔም እንዲፈጠር ያደርጋል። ስለዚህ የመሣሪያን አስከፊነት በተለይ የሕገ ወጥ መሣሪያ ዝውውር መቆጣጠር የሚያስችል የራሳቸው የሆነ ስልት መከተል እንደሚችሉና እንደሚጠበቅባቸውም ይህ ስምምነት ያረጋግጣል።*

*አባል ሀገራቱ ይህን ሕገወጥ እንቅስቃሴ የመከላከልና ስምምነቱንም የማክበር ግዴታ አለባቸው። መንግሥታት ሕገወጥ የጦር መሣሪያዎችን የሚይዙበትን ትክክለኛ መንገድ ዘርግተው መሰብሰብ አለባቸው። የመሰብሰቡ እንቅስቃሴ በመጀመሪያ ኅብረተሰባችንን መሠረት ያደረገ ትምህርት ከመስጠት መጀመር አለበት ይህም እነዚህ ሕገወጥ መሣሪ ያዎች በተለያየ መንገድ በግለሰቦች እጅ ሊገቡ እንደሚችሉ ለማሳወቅ ይረዳል።*

*በሕገ ወጥ የጦር መሣሪያዎች የሚደርሰው ውድመት ለሕይወትና በተለያዩ መሠረተ ልማቶች ላይ እያሳደረ ያለው ተፅዕኖ እንደቀላል መታየት የለበትም። ከዚህ አስከፊነቱ በመነሳትም መንግሥት በጦር መሣሪያ ቁጥጥር ሥራ ላይ ለተሰማሩ ባለሙያዎች ተግባራቸውን በብቃትና በጥራት እንዲወጡ የሚያስችል ሥልጠና በየደረጃው ሰጥቷል። እነዚህ ባለሙያዎች የሕገወጥ የመሣሪያ ዝውውር ሊከሰትባቸው የሚችልበትን ቦታ ጥናት ለማድረግ ተመድበው ውጤታማ ሥራ እየተሠራ ይገኛል።*

*በዚሁ በያዝነው ሳምንት ውስጥ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በኬንያ ውስጥ የገባችውን ቃል በቆራጥነት እያከናወነች መሆኑን የሚያረጋ ግጥና በአባል ሀገራት አርአያ መሆን የሚያስችላት ሥራ ፈጽማለች በዚህ ሳምንት ከ17ሺ በላይ ሕገ ወጥ መሣሪያዎችን አቃጥላለች። ከሕዝቧ ጋር እጅና ጓንት ለመሆን ፀረ-ሕዝብ እንቅስቃሴ ለመከላከል የሚያቂረጥ ሥራ መሥራት ይጠበቅባታል። መንግሥት ይህን ወጥ የመሥሪያ ዝውውር ዓመታዊ የሆኑ ቀዳዳዎችን ለመድፈን ያለሰለሰ ጥራት ማድረጉንም ሕዝቡን በተሻለ መንገድ በንቃት እንዲሳተፍ የደርገዋል።*

*ሕዝብ የነቃ ተሳትፎ መደረጉ ራሱን ከስጋት ነፃ ያደርገዋል። ከስጋት ነፃ መሆን የሚቻለው እያንዳንዳችን ከራሳችን በምንጀም ረው ተግባር ነው። ይህን ካደረግን የአካባቢን ሰላም ማረጋገጥ፣ ማን ምን ዓይነት ሕገወጥ እንቅሰቃሴዎችንና ፀረ-ልማትና ዴሞክራሲ አካሄድን በማከናወን ላይ መሆኑን መገንዘብ አይሳነንም። ይህ ማለት ደግሞ ለራሳችን ደህንነት ዘብ መቆም ነው።*

*ሕገወጥ የጦር መሣሪያዎችን በተለያዩ መንገዶች በግለሰቦች እጅ መግባቱን በተለያዩ አጋጣሚዎች በተከሰቱ ለወደሙ መሠረተ ልማቶች መንገዶች ብዙዎቹ ድህነትን መሠረት አድርገው ሕገወጦች ንፀሀን ዜጐችን የሚያሰ ማሩበት ሂደት ነው። ቀደም ብሎ እንደተገለጸው ድህነት የሚቀርፈው ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማትን ስንከተል ስናሰፍን ብቻ መሆኑ ሊያጠራጥረን አይገባም።*

*መንግሥት ኅብረተሰቡ እጁ ሊገቡ የሚችሉትን ሕገወጥ መሣሪያ ከሚያስከት ሏቸው ውድመት በመነሳት ዘላቂ የሆነ የግን ዛቤ መስጨበጥ ሥራዎችን ከመቼውም ጊዜ በበለጠ አጠናክሮ መሥራት ይጠበቅበታል። ሕዝቡም የገፈቱ ቀማሽ ራሱ መሆኑን*

ተገንዝቦ ለዚህ ዘመቻ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ አለበት። በድምር ሲታይ ለመሠረታዊ ፖሊሲዎችና አቅጣጫዎች ላይ በይፋ መወያየት በጉዳዩ ላይ አንድ አገራዊ የጋራ አመለካከትና እምነት እንዲይዝ ማድረግ ከጉዳቱ ጥቅሙ እጅግ የላቀ ሆኖ ይገኛል። በመሆኑም ሕዝቡ በጉዳዩ ላይ የጋራ ግንዛቤ መያዝና ባለበት ለአፈፃፀሙ የየበኩሉን አስተዋፅኦ ማበርከት ይገባዋል።

ይህን ሀገራዊ ስሜት በእያንዳንዳችን ከረፀ ለነዚህ ፀረ-ልማትና ፀረ-ሰላም ኃይሎች ቦታ አለመሰጠታችንን እኛው ልናረጋግጥ እንችላለን። በመሠረቱ አገራዊ ሕልውናን የማስጠበቅ ጉዳይ ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነው። የደህንነት መጀመሪያውም መጨረሻው አገራዊ ሕልውናን ማረጋገጥ ነው። ከብሔራዊ ጥቅም አኳያም መነሻውና መድረሻው አገራዊ ሕልውና ከተረጋገጠ በኋላ ነው። ከሁሉም ነገር በላይ አገራዊ ሕልውናን ለማረጋገጥ የተቀረፀው የውጭ ጉዳይና የደህንነት ፖሊሲያችንንም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው።

ሀብታሙ ስጦታው

አዲስ ዘመን, ህዳር 17/1999 ዓ.ም